# ትችቴ “ለቤተ አማራ ወኪል” በጀርምን የአማራ ማሕበር ሕዝባዊ ስብሰባ ስለአደረገው የመገንጠል ቅስቀሳ

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮፕያን ሰማይ)

ተከታታዮቼ ሰላም እንደምን ሰነበታችሁ። ወደ ርዕሴ ከመግባቴ በፊት እንደተለመደው አንድ ሁለት ነገር ማለት እፈልጋለሁ። መጀመሪያ በርካታ ወንድሞች እና እህቶች ዛሬም ያለማቋረጥ ስለ አዲሱ መጽሐፌ አንብባችሁ ደስታችሁን ለገለጻችሁልኝ ወገኖች አመሰግናለሁ። ከነዚህ ውስጥ ወ/ሮ ጸሐይ የተባሉ እህት ከመኔሶታ ስለ ላኩልኝ የማበረታቻ እና የደስታ መግልጫ ካርድ በተመለከተ አጠፋውን አመሰግናለሁ ለማለት ፈልጌ ስልክዎን ወይንም ኢመይልዎን ስላልጻፉበት እባክዎን ስልኬን በመደወል ያነጋግሩኝ ወይንም ኢሜይል ያድርጉልኝ ፤ እጅግ እጅግ በጣም እጅግ አመሰግናለሁ። እንዲሁም ከእስራል እና ከመሳሰሉት የላካችሁልኝ ደስታ መግለጫ አመሰግናለሁ። እባካችሁ ተመልሼ የምደውልበት ወይም የማገኛችሁበት መንገድ እንዲመቸኝ ስልክ ወይንም ኢመይላችሁ ማስቀመጥ አትርሱ።

በአንድ ጉዳይ ለመተቸት ስዘጋጅ፤- አንድ ወዳጄ በኢመይል፤ “የጀርመኑ አማራ ሕብረት ስብሰባ” እንዳዳምጥና የተረፈችህን ስስ አንጀትህን ሳታቃጥል ቤተ አማራ ስለተባለው አንድ የድሮ ጦር “የሻምበል” ማዕርግ ያለው ተናጋሪ ስለ አማራን የመገንጠል ፕሮፓጋንዳውን በትዕግስት አድምጥ ብሎ በመግለጽ እዛው ውስጥም የኔን ስም አንስቶ ሲወራጭ የሰማውን ወዳጄ ልኮልኝ፤ ስለ ሌላ ጉዳይ ለመተቸት ያሰብኩትን ሃሳቤን ለውጬ በዚህ “አዲስ- የአማራ ተገንጣይና አስገንጣይ” ግለሰብና መሕበር (ቤተ አማራ) አንድ ለማለት ወሰንኩኝ። የአማራ ማህበር በጀርመን ህዝባዊ ስብሰባ https://youtu.be/tyLzVCfC7E4

መጀመሪያ በቀና መንፈስ ተነሳስተው ጠበቃ ላጣው የአማራው ሕዝብ ፍትህ ለማስገኘት ሲሉ የጉባኤውን አዘጋጆቹንና እና ይህች ከተናጋሪዎች መሃል ያየሁዋትን ከዚህ በታች ያለቸው ውብ ታጋይ እና ድንቅ ኢትዮጵያዊት አርበኛ ከልብ ላመሰግናት አወዳለሁ። ስሟን አላወቅኩትም፤ ግን ለማሕበርሽ እና ለአንጪው ያለኝን አክብሮትና ምስጋናየ ይድረስሽ። ስምሽን ባለማወቅየ ይቅርታ።

ይህ ሰው ሻምበል መርዕድ” ይባላል። የቤተ አማራ ተናጋሪ ነው። ኤርትራና ትግራይ ነበርኩ ህይወቴን በጦር ሰራዊት ያገለገልኩኝ ነኝ ብሎናል። ለምን ለማድረግ ብላችሁ በትጠይቁት መልሱ “ዳር ድምበር ለማስከበር” ነው። አሁን ያ ተዋጋሁለት የሚለንን ዳር ድምብርና ሕዝብ “ሕዝቤ እና ድምበሬ አይደለም ፤ኢትዮጵያ የሚባል አገር አላውቅም ከዚህ ወዲህ ድምበሬና ሕዝቤ ቤተ-አማራ የሚባል አገርና ሕዝብ ነው” በማለት አማራ የሚባል አገርና መንግሥት መስርቶ ሌሎቹን “ደካማዎቹን” ከስሩ በማድረግ “ ለመርዳት ”እንደሚችል ነግሮናል። ይህ ተምበርካኪነት፤ ተሸናፊነትና ጠባብ ብሔረተኛ ተገንጠይነት የተማረው ደግሞ ወያኔ ለ26 አመት በበወዘው የሕሊና ዉጤት መሆኑን የነገድ ፖለቲካ የተከታተላችሁ አዋቂዎች አትስቱትም። በአዲሱ መጽሐፌ ውስጥም እንደገለጽኩት እንዲህ ያሉ ሰዎች በወያኔ እና በኦነግ የኮሚኒስቶችና የጣሊያኖች ሴራና የመገንጠል ቅስቀሳ ለ26 አመት ተበክለው፤ የአገር ትርጉም መላ ቅጡን በታትነው “ በተበደለና ል መፈክር ስም ” (በቪክቲማይዜሽን ሰሎጋን) ሽፋን ስር አገር እና አንደነትን በማፍረስ ብጥብጥን በማስፋፋት፤ እንደዚህ ሰውዬ የመሳሰሉ “ወታደሮች” ሳይቀሩ በስሜት የተበከሉ አደገኞች የሆኑ ፋሺስቶች ወደ መድረኩ ብቅ አንደሚሉ ጽፍያለሁ። ያንን በዶክተር አሰፋ የተተነተነና ብቸኛ ጥናት ደጋግማችሁ በደምብ አኝኩት። የዚህ ሰውየና ተከታዮቹ አይነት ሰዎች ባሕሪ በዛው ጥናት በደምብ ታገኙታላችሁ እና አፈላልጋችሁ አንብቡት። ፋሺስትነት የትምክሕት ርዕዮት መመሪያ ስልት ነው። ነጭ ጥቁር፤ቢጫ…እስላም ክርስትያን… ማንኛውም “ፋሺስት” ይሆናል።

ይህ ሻምበል እና ድርጅቱ (ቤተ አማራ)፡ በፋሺስት ፈለግ በመጓዝ ኣእምሮው የተበወዘ ብቻ ሳይሆን የወያኔ ቅጥረኛ እና ሰርጎ የገባ በአማራ ስም አማራን ለማበጣበጥ የተላከ ሰው ነው ብለው የሚሉ ሰዎች ከሰማችሁ የተሳሳቱ ሊሆኑ አይችሉም ይሆናል። ምክንያቱም የወያኔ ሰላዮች የነበሩ በቃለ መጠይቆቻቸው እንደነገሩን (በየድረገጹ እንደተለጠፈው) ሲነግሩን፤ ተልዕኮአቸውን ለመፈጸም “እስር ቤት ገብተው በገራፊዎች ሁሉ ሲደበደቡ ያንን ችለው አብሮዋቸው ከታሰሩና ከተደበደቡ ‘አስፈላጊ’ እስረኞች

የተፈለገው መረጃ ለማግኘት እራሳቸው በመደበቅና ታጋዮች በመምስል ከገዛ መንግሥታቸው/ድርጅታቸው/ የማሳሳቻ ስቃይ ሁሉ እንደሚደርስባቸውና አካባቢያቸውን ለማሳሳት ተበዳይ መስለው ስራቸውን እንደሚሰሩ የተረጋገጠ ነው። ይህ ሰውየ እና በቤተ አማራ የተባለው በፋሺዝም የተበከሉ አዳዲስ አማራ ፋሺስት ወጣቶች ሰርገው ለአፍራሽ ሃይል አለመስራታቸው ማንም ሰው "በእርግጣኛነት" መናገር አይችልም። ትችላላችሁ? ማንም ሰው አዎ ሊል አይችልም። ከዚህ ውጭ 'ቅጥረኛ ካልሆነም' ባለፈው ሁለት ሰሞን ትችቴ በትግሬ ሁለት ምሁራን ፋሺስቶች እንደተቸሁት ሁሉ ይህ ሻምበል እና ድርጀቱ አማራነትን የአማራ ማሕበረሰብ እሮሮን በመንተራስ "ፋሺስታዊ' ርዕይቶት የሚከተል አዲስ "ውጥን" ነው መለት ነው። ከሁለቱ ትንታኔዎች አንዱ ነው ማለት ነው።

ፋሺዝም የሚቀሰቅሱ "የተማሩ" ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በግድያ ተግባር ያለፉ፤ ሰው በመደብደብ ልምድ ያለፉ፤ የሰው ደም ሲፈስስ ቀን ተቀን ሲያዩ የነበሩ፤ ሲገድሉ የነበሩ ወታደሮች፤ሲቪሎች፤ ግፍ በመስራት ያለፉ ወይንም ሲደረግ ለበርካታ አመታት የተመለከቱ "ዱርየዎችም" እራሰቸውም ሲገረፉ የነበሩ፤ ጭምር የሚያስተጋቡት ወይንም የሚመሰርቱት 'ተስፋ በቆረጡ' ደካማዎችና የትምክሕተኞች ርዕዮት ነው። ይህ ግለሰብ እንደነገረን ከሆነ ለማደራጀት እስከሚቸግረን በሺዎቹ አማራ ወጣቶች እየተመዘገቡ ነው ሲል ትንሽ ብያስቅም ፤የሚያስገርም አይሆንም። ምክንያቱም የፋሺሰት ርዕዮት የሚያራግቡ ቡድኖች/ግለሰቦች/ የሚሞረኮዙት በግፍ የተጠቃውን ማሕበረሰብ በመቀስቀስ ብስለቱንና ወቅቱን ገምግመው በስስ ብልቱ ገብተው ባጭር ወቅት በስሜት በማስጨፈር ብዙ አባላትን ከጎናቸው ማሰለፍ ይችላሉ (ወያኔም ፤ሂትለርም፤ ሙሶሊኒም፤ "ዳዕሽ' (አይ-ሲስ የተባለው እስላማዊ ጽንፈኛ..ያደረጉት ያ ነው፤ እንዲሁም የሶማሌው አልሸባብም፤ አግም፤ ኦብነግም፤ወያኔም፤ ሻዕቢያም......)። በሺዎቹ ማስከተል ይችላሉ። ሰውየው እንዳለው እና ፏሲቶችም እንዳየናቸው፤ "በነገድ" ቀስቅሶ ሚሊዮኖችን ማስከተለው በጣም የሚቀል የድርጅት ስራ ነው።

ፋሺዝም ለመመስረት ትምህርት አይጠይቅም። የሚጠይቀው የተገፋውን ማሕበረስብ የድሮ ሃያልኑና ሓብታምነቱ ታሪክ ሰሪነቱ በማውሳት ተበድለሃል በሚል፤ አሁን ባለው የድህንት አዘቅትና ውርደት እንዴት እንደገባ እና ፤ ለዛውም በመደራጀት ያንን ሃያልነቱን መልሶ ለመጨበጥ፤ ድርጅቱን ቢከተል የነበረውን 'ማርና ወተት" ማስመለስ እንደሚችል፤ ሌሎችንም በስሩ አስሰልፎ (ልክ ይህ ሻምበል እንደነገረን) የራሱን ነገድ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹ "አናሳ/ደካማ ነገዶችንም ጭምር ነጻ አውጥቶ ሊመራቸው እንደሚችል መስበክ ብቻ ነው የሚፈለገው የጨዋታው ሕግጋት።

ያ ካደረገ ሺዎቹን በጥቂት ጊዜ ማስከተል ይቻላል። እንዳያችሁት በቪዲዮው ላይ የሚናገሩት የሚያንጨበጭቡ አድማጮችና ወደ መነጋገሪያው በመጠጋት ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበሩት ወጣቶች በስሜት የተነዱ፤ ምን እንደሚሉ ያልገባቸው፤ አማራ እና ኢትዮጵያ፤ ለፍትሕ መታገልና መንግሥት መመሥረትን ያለው ልዩነት ምን መሆኑን ያልገባቸው ብቻ ሳይሆኑ "ኢትዮጵያ ለኛ ለአማራዎች በድላናለች ፤ጠላታችን እንጂ ወዳጃችን አልነበረችም፤ የጠቀመቻችሁ እንደሆነ ለ60ዎቹ ለናንተ እንጂ አዲሱ ትውልድ አናውቃትም "አየራሳችን አገር እንመሰርታለን" ። የሚል አንድምታ ነው ያደመጥኩት። ይህ ቴነደንሲ /ይህ ቁዘማ / የፋሺስቶች የመጀመሪያው የሽሽትና የባይተዋርነት ስሜት ነው። ፋሺዝም ለመማር የሚጥር ሰው ከነዚህ የወጠቶች 'ቶን'የሚወጣው "የባይተዋርነት-ልሳን" በቀላሉ መተንትን ይችላል።

አገር ከመሰርቱ "አማራ የሚኖሮው እና ጂኦግራፊ ቦታው" የት እና እስከ ነው ሲባሉ መልስ የላቸውም። መላው ኢትዮጵያ ከሆነ ደግሞ "አዲስ አማራ የተበለ አገር የት እንደሚመሰረት አልነገሩንም"" እዛው ኢትዮጵያ መላዋ ምድር ከሆነም፤ ሌሎቹን ደፍጥጦ የአማራ አገርና መንግሥት ከሆነም "አሁን የምላችሁ "ፋሺዝም" ነው። ኢትዮጵያ መባልዋ ቀርቶ "አማራ/ቤተ አማራ/ ልትባል፤ ወይንም የአማራ አገር ተብላ ልትጠራ ነው"። ጨዋታው ስትተረጉሙት፤- የፋሺስቶች፤ የልጆች ጨዋታ፤ የወያኔ እና የኦነጎች የፖለቲካ "ብከላ" ነው። ወደ እዚህ የዘቀጠ የተሸናፊነት መፈክር ሲገቡ የቻሉት፤ ግፉ እና የፖለቲካው ወላፈን ፊት ለፊት መጋፈጥ ስላልቻሉ የመሸሺያ "የመሸነፍ ምልክት" ነው። ወያኔዎች በመጨረሻ ሲሸነፉ፤ ወላፈኑ አላስቆም አላስቀምጥም ሲላቸው "ትግራይ ትግርኚን" ግንጠላ በተጠባባቂ "የመሸሺያ ስልት" እንደጠበቁት ማለት ነው።

የቤተ አማራ ሰውዬው በዚህ አላበቃም። ሞረሽ ወገኔ የተባለው 'የማሕበረሰብ ነክ" ድርጅት እንዴት እንደሚያብለጠልጡት የሰዎቹ ባሕሪና ብስለት ማየት የማሕበረሰቡ ንቃት ደረጃ ወዴት እየዘቀጠ መሄዱን የታዘበኩነት ትምህርት ነው። እጅግ ቀኝ አክራሪው የፋሺስቶች ክንፍ በስሜት የሚነዱ "እኛ እና እነሱ" በሚል የታጠሩ፤ ያልተገሩ ጎስታፖዎችን (መቺ-ሃይሎችን) በማሰማራት/በመፍጠር/በመቀስቀስ/ "የራሰችን እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን" እስከማለት ይደርሳሉ (የመንግስቱ

ሃይለማርያም ባህሪ በሻለቃ ፍስሃ ደስታ የተገለጸው ታሪክ አንብቡ)። ልክ አንድ የቤተ አማራ ወጣት እዛው በአማራ መሕበር ስበሰባ አዳራሽ ውስጥ ሌሎቹን "እርምጃ የመውሰድ" የማስፈራርያ ቀለበት ውስጥ ለማስገባት እንደቃጣው ባሕሪ ማለት ነው። ትንንሽ ሰዎች በጣም አደገኞች እና ካፍንጫቸው አርቀው ስላማያዩ በሕዝብ ላይ የሚከተለው ጦስ አይገነዘቡትም፤ ቢገነዘቡትም በራሳቸው ላይ ሲደርስ ብቻ ነው። የቤተ አማራ መሪዎች እና ደጋፊዎቹ ወደ አዳራሹ ከመግባታቸው አስቀድመው በጥናት የሰሩት ጸረ ሰብሳቢዎቹ እና የራዲዮን አዘጋጆችም ሳይቀር ለመጋፈጥ አቅደው እንደመጡ ከደጋፎወቻቸው አነጋገር በቀላሉ ማወቅ ይቻላል። ሌላኛው ወገን ተቅለስልሶ ተለሳልሶ ባይዛቸው ኖሮ ባየሁት የወጣቶች አመጣጥና ድፍረት ውጥረት ውስጥ ይገቡ ነበር። አያችሁ እንዲህ ያሉ ወጣቶች በስሜት ስለሚገፉ የግንጣላ ደጋፊዎችን ማፍራት በጣም ቀላል ነው። መሳፍንት የተባለ የቤተ አማራ ምክትል መሪ (?) ዋሺንግቶን ስብሰባ ተደርጎ ይመጣል ሲባል፤ ስብሰባውን ረግጠው የሄዱ ሰዎች ሰምተናል እናንተ ደግሞ.......ሲል ፍጥጫ ያማረው ወጣት ነበር። እንዲህ ያሉ ሰዎች ፖለቲካ ሳይሆን ስብሰባን ረግጦ የመውጣት ትዕይንት የፖለቲካ መቃወሚያ አንዱ ስልት መሆኑን አልገባውም። አማራን እና ኢትዮጵያን እናፍርስ እንገንጥል ስንል ለምን አልጋ ባልጋ አልሆነልንም ነው የዛ ምስኪኑ ወጣቱ ጥያቄ ።

ፋሺዝም ምንድነው? ለምትሉ ከጥቂት ወራቶች በፊት ጀርመን ውስጥ በዶ/ር አሰፋ ነጋሽ የተደረገ ንግግር በወልቃይት ድረገጽ ስለሚገኝ ቪዲየው ይገኛል እዛው አድምጡት። ለማንበብ ከፈለጋችሁም በአዲሱ መጽሐፌ ውስጥ በስፋት ተዘርዝሯል። ይህ የሻምበልነት ማዕረግ ያለው "ሻምበል ማዕርጉ" የተባለው ግለሰብ የሰነዘረው ንግግር አንዱን ልጥቀስ? እኛ አማራዎች የራሳችንን መንግሥትና አገር መስርተን "እናሳ ብሔረሰቦችን" ሁሉ መብት ማስከበር የምንችል ሃያል ሕዝብ ነን" ይላል። ይሄ ከወያኔ ትግሬዎች ፋሺዝም የሚለይበት ምክንያት የለውም። አይደለም እንዴ? ትልቁ ትንሹን ትንሹ ትልቁን እየተለዋወጠ እንዳሰኘው ሃያልነቱን በመስበክ ሌላውን 'ደካማ' 'ደንቆሮ' ራሱን ማስተዳደር' 'ራሱን መርዳት' የማይችለውን በኔ ሃያልነት ነፃነቱን፤መብቱን ዕርዳታውን ያገኛል የሚለው በጣሊያኖች፤በትግሬ ወያኔዎች፤ በሻዕቢያዎች፤ በኦሮሞ ተገንጣዮች (በነ ሌንጮና ዳውድ) ንግግሮች የተደመጠ ፤የተጻፈ ባሕሪ ነው። አይደለም እንዴ? ጃዋር መሐመድ እንኳ ባቅምዋ "የአበሻ/የአማራ/ ሚዲያዎች እኔን ካላስተናገዱ አይሆንላቸውም፤ ካለ እኔ የፖለቲካ ተንታኝ ሌላ የራሳቸው የላቸውም፤ ለዚህም ነው አስሬ የሚጋብዙኝ፤ ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኦሮሞ ሕዝብ በልጁ በጃዋር መሃመድ መኩራት አለበት" ሲላቸው ኦሮሞዎቹ አዳራሹን በጭብጫባ አቅልጠውታል። ስለሆነም ዛሬም "ኢትዮጵያ ከኦሮሞ መሬት ባስቸኳይ ትውጣ እንዳላለን እና ነፍጠኛ እንዳላለን ሁሉ ዛሬም እነ ቢላል ሸው፤ ሕብር ራዲዮ ዘሐበሻ ወዘተ...ያለ ጃዋር አይሆንላቸውም። ቀበሮዋ ጃዋር አልቀለደቺም፡ ንግግሯ እውነት ይመስላል። አዎ፤ ትምክሕተኞች ለከት የላቸውም። የኛዎቹም ፍከራቸው፤ የጃዋርን መንገድ ተከትለዋል። ብከላ ማለት ይኼ ነው። "ሳይጠኑ ጎፈሬ" ነው የሚባለው?

ካስገረመኝ ነገር ሌለው ደግሞ፡ የዚህ የፋሺስት አፍራሽ ድርጅት ተከታዮች ከአዳራሹ እየተነሱ የተቀሩትን የመድረኩ ተናጋሪዎችን ሲወጥርዋቸው"" ባላቸው አቋም ተጋፍጠው ድርጅታችን እናንተ የምትከተሉት አፍራሽ የሆነ የፋሺዝምን ርዕዮት አይከተልም፤ መገንጠልና አገርን ማፍረስ ከወያኔ የተለየ አይደለም፤ ስለዚህ ስትፈልጉ፤ ኦነግና ወያኔ ጋር ሂዳችሁ ስለ አዲስ አገራችሁ ምስረታ ተነታረኩ" አብረን አንሄድም፤ ከማለት እና ለወደፊቱ እንዲህ ያለ ርዕዮት ማስተናገድና አብሮ መስራት እንደማይፈልጉ ከመግለጽ ይልቅ፤ በሚገረም ለስላሳነት ባሕሪ እየተቅለሰለሱ "ማንም ድርጅት አማራ እስከሆነ ድረስ አናገልለውም፡ አብረን እንሰራለን..." እያሉ ሳደምጣቸው እኔ እራሴ በአግራሞት ተሰምጬ የምለውን ነው ያጣሁት።

"አማራ እስከሆነ ድረስ" ምን ማለት ነው?፡ በአማራ ስም የተደራጀ ቤተ አማራ "ወላጆቻችሁን እና ሌሎች ዜጎች አፈርሳለሁ እያላቸው "እሺ አማራዎች ናችሁ እና አብረን እንሰራለን" አፍርሱን፤ገንጥሉን ይላሉ። ምንድ ነው አበራችሁ የምትሰሩት? ግንጣለው ነው፤ አገር ማፍረስን ነው? ምኑ ነው አብራችሁ የምትሰሩት? ንገሩን እስኪ? ለምን ከኦነግ ጋር አትሰሩም? ኦነግ ወያኔ ይቃወማል፤ ቤተ አማራም እንደዛው፤ ልዩነታቸው ግን ያ የአማራ አገ ር፤ ያ ደግሞ የኦሮሞ አገር መመስረት ነው። " ስለዚህ ኦነግ ጋር የማትሰሩበት ኦብነግ ኦጋዴን ጋር እየተቻቻላችሁ የማትሰሩበት ምክንያት ምንድ ነው፤ ያ ከሆነ? አማራ ስላልሆኑ ነው? "የጠራ ደም" ስለሌላቸው ነው?

"ይህ ጠባብና ገንጣይ" ሻምበል ተብየው ሰውዬ "ጌታቸው ረዳ ትግሬ ነው እና ሞረሽ የተባለው ለምንድነው አባል ያደረጋችሁት?" ሲላቸው (ያውም በማያገባው የድርጅት ፖሊሲ ገብቶ እኮ ነው ደግሞ እንዲህ የሚላቸው) እነሱ ደግሞ- "አማራ ድርጅት ውስጥ አማራ ብቻ ነው አባል ሆኖ መግባት የሚችለው" እኛ ስሙን የተቀስነው ስላደረገው አስተዋጽኦ ነው የጠቀስኩት

እንጂ አባል ነው አላልኩም ስተለው ያች የተቀደሰች እህት፤ ቡራ ከረዩ ማለት ጀምሮ ማየቴ ገረመኝ። እኔ የሞረሽም የማንም አባል ባልሆንም፤ ነገሩ አስገርሞኛል። እኔ የአጋዚያን ግንጣላ ፖለቲካ ባራምድ በሳምንት ሺዎቹን ትግሬዎች እና ኤርትራኖችን ነበር የማስሰልፈው። ግን አላማየ ይህ ሰው እንደሚያወራው ስላልሆነ ብዙ ከመናገር ልተወው።

የሚገርመው ነገር፤ ሞረሽ ውስጥ የሚገባው "አማራ' (የጠራ ደም ያለው) ብቻ ነው አባል የሚሆነው እንጂ (የጠራ "ደም") ያልሆነ ማስገባት አንችልም፡ እያሉ ሲናገሩ "የጠራ አማራ ደም ከሌለህ" ምንም እንኳ ስለ አማራ ብትታገልም "ትግሬ ትግሬ ነው፤ ነጭ ነጭ ነው" ወደ እሚለው ዘረኛ ርዕዮት ገብተዋል ማለት ነው። ለከት እንዳጣው የእሳለሞቹ አሜሪካዊው ጥቁር "ሉዊስ ፋራካን" ሰዎች በደማቸው/በዘራቸው/በነገዳቸው እንጂ በተግባራቸው እና በዜግነታቸው አይታዩም ማለት ነው።

የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድን የታገለው የማንዴላ ድርጅት "ኤ-ኤን-ሲ" በጥቁሮች ብቻ አልነበረም የተገነባውና ትግሉን ያካሄደው። ሕንዶች፤ነጮችም ጭምር አብረው ሞተው፤ታስረው፤ ፖሊሲ ቀርጸው፤ታግለው ነው ለድል ያበቁት። ታዲያ የኛዎቹ "የፖለቲካ ጨጨዎች" <የጠራ የአማራ ደም> ከሌለህ ደማችን እና ድርጅታችን ትበክላለህ እና ለአማራ ሕዝብ ትግል አትመጥንም፤ ለመጮህም ከኛ ድርጅት ሆነህ አይፈቀድም" ይላሉ። ብዙዎቹ አባሎች በስሜት እንጂ የሚያስከትለው ጉድለት የተገነዘቡት አይመስሉም። በስመ አማራ፤ በስመ የጠራ ደም፤ መመልመል የፖለቲካ ደካማነት ካልሆነ ፤በአማራ ስም ተደራጅቶ "ቤተ አማራ' ብሎ ራሱን ሰይሞ አገር እና ሕዝብን አመሳቅላችኋለሁ ሲላቸው "አማራ ስለሆንክ አብረን እንሰራለን" አፈርሰን፤ በትነን፤ አመሳቅለን፤ከሌሎች ዘሮቻችን ለየን ብለውታል። አይደለም እንዴ? እነዚያ "ኢትዮጵያ" ይላሉ፤ ያ ደግሞ "ቤተ አማራ" የተባለ አገርና መንግሥት ይላል። ታዲያ አብረው ለመስራት ይሞዳሞዳሉ። ማናቸው ጓድ መንግሥቱ እኔ እየተጠበበኝ መጥቷል ያሉት መንግሥቱን "አባ ቄሱ ናቸው? የኼ ነገር ለኔም እየጠበበኝ መጥቷል።

አፓርታይድ በምንታገልብት ዘመን እገሌ ዘራችን አይደለም፤ ስለዚህም እገሌ የተለየ "ደም" እና የጎደፈ ደም፤ የጠራ ደም እና ያልጠራ ደም ንግግር መውረዳችን አጅግ ይገርማል። አማራ ካልሆነ፤ የአማራውን ግፍ የኔ ነው፤ስቃዩ ስቃዬ ነው አይልም፤ ብለው እራሳቸውን ታጋዮችና ወካዮች አድርገው፤ አማራ ያልሆነው ሲጮህላቸው፤ ለ20 አመት ሲያንቀላፉና እባካችሁ ተደራጁ ሲላቸው የነበረውን "የአማራ ወኪል ማን አደረገህ" እያሉ ሲሰድቡት የነበረውን ግለሰብ ረስተው፤ ወያኔ ወደ እሚያስተዳድራት መሬት ኢትዮጵያ እየሄዱ <<አጐቴ፤አክስቴ ለዘመናት የተለየሗት በፍቅር ናፍቆት ያመነመነቺኝ ውሽማየ፤ ፍቅረኛየ አገኘኋት>> እያሉ እንቅልፋቸው ሲለጥጡ መኖራቸውን ረስተውት፤ የተገለቢጦሽ ስለ አማራ ሲጮህ የነበረው ሰውየን "እንዴት አባል ታደርጉታላችሁ" ብሎ ዛሬ ሲንፈራገጡ ማድመጥ ከመሳቅ ሌላ ምን ማለት እችላለሁ። እናቴ መኖርያ ግብያችን ውስጥ አንዲት ወፍ በርራ መጥታ ከጥቂት ጊዜ ቆይታ መሬት ላይ በጀርባዋ ተንጋልላ ሰትደንስ አይታት፤ "ወይ ጉድ! ነፋስም ለካ ወፈቷንም ያሰክራል" ያለቺውን ነገር ዛሬ ታወሰኝ። ይኼ ለ26 አመት የነፈሰ ነፋስ ሰንት የነገድ ሰካራም ማፍራቱን ስመለከት ለመጪዋ አገሬ አጅግ አዘንኩኝ። እኔ ስደግፋችሁ ልትጠብቡ አይደለም የታገልኩት፤ ዛሬም ነገም ትናንትናም፤ ለአማራው ሕዝብ ፍትህና ሰላም ለመቆም እንጂ እንደትገነጠሉ ወይንም በትምክህት እንድትሰክሩ አልነበረም። አንዲት ጀርመን ውስጥ የምትኖር "ጸሀፊ' ነኝ የምትል በዘሃበሻ ሰሞነኛ የነበረች ሴት "ብርሃኑ ነጋን ተጋፈጥክ" ብላ እኔኑን 'በጠጣራ አማርኛዋ" ጌታቸው ረዳ ወያኔ ነው እያለች ስትዘልፈኝ ነበር። ዛሬ ተመልሳ ስለ አማራ፤አማራ እያለች ስታወራ ስሰማ አማራን የሚጠላውን የድርጅት መሪ የሚካካውን ሰው ወዮላችሁ "ሞቼ ብገኝ" ስትል የነበረቺውን ሴትዮ እንኳን ወደ ልቦናሽ ተመለስሽ ነው ያልኩት። አሁን ደግሞ ይሕ 'ክቡር ሻምበሌ' ጌታቸው ረዳ ለምን ብሎ ሞረሽን ሊያፋጥጥባቸው ሳደምጥ ሰምቼው ይህ ሰውዬ ቀንቶት አዲሲትዋን "ቤተ አማራ" አገር ቢመሰርት ትግሬ ስለሆንኩኝ ብቻ "በ24 ሰዓት" ወደ አገሬ ኢትዮጵያ ያባርረኝ ነበር ማለት ነው።

እውነት ለመናገር ገንጣዮቹ አማራ የምትባል አገር ከመሰረቱ በኋላ ይቅር፤ አሁን አማራ በሚፈልጋቸው ወቅት እንኳ እራሳቸው በምድሪቱ መሬት ሄደው ጠላቱን ለመዋጋት አልደፈሩም። አዳራሽ ውስጥ ገብተው ግን "እስከ መጨረሻ ድረስ አማራን ለመገንጠል አንዋደቃለን" እያሉ ሲፎክሩ መስማት የሚያስቅ ቢሆንም የሞያናድድ ቅጥፈት ነው። ዛሬ በመከራው ያልኖሩበት፤ ገንጥለው አዲስ አገር ለመመስረት ስንት ጉድ እና ሂደት የሚያልፈውን የግንባታ እና የስቃይ ሂደት ከዚህ ኑሮአቸው ተላቅቀው ሄደው ይኖሩበታል ማለት የልጆች ትረካ ነው። እውነት ነው አይደለም እንዴ? ሕዝቡ ኑ የት አላችሁ? እያላቸው እራሳቸው ከዚህ ኑሮ አላቅቀው ወደ ምድሪቷ ጫካ ሄደው ጠላታቸውን መፋለም አይፈልጉም። የሚነግዱት ንግድ፤ እዛው አገር ባሉት በጥቂት ቆራጦች ላብና ደም እዚህ ሆነው "እኛ ነን የምናደርገው፤ ይኼው...ወዘተ......ካልሆነ "ሂዱ ቢባሉ አይሄዱም። እነዚህ ወጣቶች ናቸው በየአደራሹ ማይክሮፎን ይዘው የሚጮኹ፤ ሽማግሌዎች አይደለም። ይሄ ደግሞ ሻምበል ነው ወታደር፡ እዚህ ምን

ያደርጋሉ? አገር ለመመስረት ከፈለጉ ጫካ ሄደው እንደ ነፃ አውጪዎች ድንጋይ ላይ መተኛትና መሬትን ነፃ ማውጣን እና “ቤተ-አማራ’ አገር መመስረት ነው። አይደለም እንዴ?

ልክ የግንቦት 7 ፓል-ቶክ አንጨብጫቢዎች ወጣቶች ናቸው። ከነኚሆቹ አንድ ባሕሪ አላቸው። ብርሃኑ ነጋ ወደ ኤርትራ ኑ ተከተሉኝ እዛው ትቼአችሁ አስመራ ሆኜ እከታተላችኋለሁ ሲላቸው አይሄዱም። ሞኝህን ፈልግ ነው የሚሉት። ብርሃኑ እራሱ፤ ንአምን ዘለቀ፤ እዮኤል...መሳይ፤ፋሲል አበበ..ወዘተ ወዘተ.....ሁሉም ለጉብኝት ነው አስመራን እየተሳለሙ የሚመጡት። እኔ በወጣትነቴ ትግል የማውቀው ጫካ ሄዶ ወይንም ከምታምንበት ወገን ሆነህ በነፍጥ መፋለም ነው የማውቀው። ዛሬ በየ አዳራሹ እየቦተለኩ፤ አስመራ ደርሶ መልስ መሪዎቹም አዝማሪውም፤ጋዜጠኛውም ምኑም.. ጀሌውም “ሳውዲ አረቢያ “ለሃጅ” እንደሚሄዱ ወቅታዊ ተሳላሚዎች ይመስል ኤርትራ ሄደው ደርሰው ይመጣሉ። ኰምብሽታቶ “አደይ ስላስን” “ዓደይ ኢታይን” በረከት መንግሥተ አብን፤ ጓል ተበርህን፤ ጓል ጸሃይቱ በራኺን አግኝቼአቸው ተላቀስን ፤ወዲ ትኩልን አገኘሁት፤የረሳሁትን ሜሎቲ ቀመስኮኝ፤ “አንዲት ሽማግሌ ከየት ነህ ወንድሜ ብለው በተሰባበረ አማርኛና በትግርኛ ሲያነግሩኝ ሆዴ ሁሉ ባባ..... አልቅስ አልቅስ አለኝ .....መሃረምየን ረስቸው እንጂ ላለቅስ ትንሽ ነው የቀረኝ፤....እያሉ ሲመለሱ ልብ ወለድ ትረካቸውና ያሳለፉት መልካም ወራትና ሰምንት ይተርኩልናል። “ወጣት” ጋዜጠኞች የሚታረድ የሉካንዳ በሬ ይመስል ቦርጫቸውና ቂጣቸው መሸከም እቅቷቸው መሳቂያ ሆነው ‘ትንሸየዋን ጉብታ” መውጣት አቅቷቸው ሻዕቢያዎች እንደ ደከመ አህያ ቂጣቸውን ደግፈው እየገፉ ሲያስወጣቸው የሚያሳይ ቪዲዮ እንድንመለከትላቸው በሚዲያ ይለቁታል። አስገራሚ ዘመን! ትግል ማለት ይኼ ነው!

አገር እኮ በደም መተሳሰር በመለሳለስ አይደለም የሚገነባው እና ፖለቲካውም የሚሰራው። ቤተሰቦቻችሁን እንገነጥልላችኋለሁ፤ ምትስማሙ ወደ እዚህ የማትስማሙ ወደዚያ ማዶ ይሂድ፤ አፈርሳችኋለሁ ሲላቸው “አማራ እስከ ሆነክ ድረስ እሺ አብረን እንሰራለን እያሉ ሲለሳለሱ አድምጩ” እኔ የምለው ነው የገረመኝ።

መስፍን ውልደማርያም እዛው አገራችሁ ስትፍልጉ እዛው መቀበሪያ ፈልጉ እንጂ አገራችን አናስቀብርም ያለንን ያህል እኮ ነው። ኢትዮጵያ የኛ እንጂ የናንተ አይደለችም ይለናል ፕሮፌሰር መስፍን። እነዚህም አማራ የሚባል ሕዝብ እና መንደር የአማራ ብቻ አድርገው የማየት ማን ነው ያስተማራቸው? አማራ ላንተ ምንምህ አይደለም የማለት መብት ማን ነው የሰጣቸው? አማራ ማለት፤ ኢትዮጵያ ማለት የዘመናት መስተጋብርና የሕዝቦች ድብልቅ ንብረትና የሕዝብ ደም ውርርስ መሆኑን እነዚህ ወንድሞች አላወቁትም። እነኚህ እነማን ይባላሉ እንገነጥለዋለን ብለው የሚዝቱበት መሬትና ሕዝብ የኛ ብቻ ነው የሚሉን? መብቱ የሰጣቸው ወያኔ ነው? ወያኔን እንደተዋጋነው እኛም እኮ እናንተንም እንዋጋችኋለን? ወያኔ ከናንተ በምን ይለያል? ለ26 አመት በብረትና በሚዲያ የታገልነው እኮ የመገንጠልና የፋሺዝም ርዕዮት በማስፋፋቱ ነው። ማን ነው የናንተ አማራ የሚባል ሕዝብ እና መሬት የጌታቸው ረዳም የትግሬውም የሌለውም አይደለም ብሎ የነገረህ? ምን እሚሉት ትምህርት ነው?!

አማርኛ መናገር አማራ ነው ማለት አያሰኘውም ብሏል፤ ሌሎቹን ሲያጣጥል እሱ በንጹህ አማራነት ሲፎክር ሻምበሉ። አንተም አማርኛ በመናገርህ ብቻ ነው እያደመጥንህ ያለው እንጂ ማንነትህ በምን ላብሮቶሪ ተመርምረህ ነው አማራ ነው ብለን የምንቀበልህ? ምን የዘር ክርክር ውስጥ አስገቡን? ለመሆኑ አማራ የሚባል “ዲ ኤን ኤስ” አለ? አንድ ሰው አማራ ነኝ፤ትግሬ ነኝ ወዘተ.... ካለህ አንተ አማራ አይደለህም ትግሬ አይደለህም የማለት መብት የለህም!!!!! መብት የላችሁም! የሚገርም ነው። የምናውቀውን የ26 አመቱ ወያኔ እንዳንታገል ይኼ ሁለተኛ ዙር አዲስ ወያኔ በየት በየት ዞሮ መጣብን?!!!!!

ወዳጄ አማራ ብሻው “የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፉ በገጽ 91 ላይ እንዲህ ይላል፡-

<<ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 8 ቁጥር 6 ጥር 1993 ዓ.ም ገጽ 31 “ወያኔ መሪዎችና ለደጋፊዎቻቸው ያልተገለጸላቸው ወይም ሊያጤኑት ያልደፈሩት ሐቅ በአካባቢው ያሉት ብልጦች እነሱ ብቻ አለመሆናቸውን ነው። ስለዚህ ሰዶ ማሳደድድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ እንደሚሉት የእጃቸውን ለቀው አሻግረው ሌላ መመልከታቸው ግብዝነት ነው። አንድ አገር እንደ አገር ለመቀጥል ከፈለገ ሊንከባከባቸው የሚገባቸው ዛላቂና ቋሚ ጥቅሞች ሊኖሩት ይገባል። ከነዚህ ዓይነተኛው ምክንያቱንና ቋሚ ሉዓላዊነቱን የሚያረጋግጥበት ዳር ድንበር ነው። ይህ ዳር ድንበርና በርሱ ውስጥ የተካለሉት ሃብቶች የአንድ ትውልድ ወይም በአንድ ወቅት የወጣ የአመራር ቡድን ንብረት አይደለም። እነዚህን ዘላቂ ጥቅሞች በደረስንበት ጊዜ የመጠቀም እንጂ አሳልፈን የመስጠት መብት የለንም።” ይላል በገጽ 91 (አማረ ብሻው)። አዎ ቤተ አማራ የተባለው ገንጣይ እና ሴረኛ ቡድን የአማራ ሕዝብም ሆነ መሬት እንዲገነጥል አንፈቅድለትም። የማስገንጠልና የመስጠት መብትም የለንም፡፡እሱም የለውም።

ጽሑፌን ልደምድም፡

የፋሺስት ርዕዩት ስልጣኔ መስሎአቸው ሕዝብን ለማባላትና አገርን ለማፍረስ የሚሯሯጡ በስሜት የሚጋልቡ ሰዎች ልነግራቸው የምፈልገው…. ..’ከወንጀሎች ሁሉ የከፋው ወንጀል የራሱን ዘመን ብቻ ሳይሆን የሚመጣውንም ትውልድ ዕድል ማበላሸት የከፋው የወንጀሎቹ ቁንጮ ነው። ከዚህ ወንጀል መጽዳት አስፈላጊ ነው። ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ በዚህ ሴራ እና የግንጣላ “ሳብሸርዢን” (ብከላ) ተበክለው ዛሬው ያለውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የመጪውንም ትውልድ ሕዝብ ዕድል እየበላሹት መሆኑን ለማወቅ አያስቸግርም። ቤተ አማራም ሆነ ከዚህ ቡድን ጋር የሚለሳለሱ ማሕበሮች እና ግለሰቦች ሕዝባቸውን ለዳግም መከራና ግጭት አገር ላገር ፤መንደር ለመንደር እንዲጎተትና በጠራ የዘር ፖለቲካ እንዲባዝን ለማድረግ ከሚጥር ከፍተኛ ወንጀል ለመፈጸም ከሚዝቱ ግለሰቦችና ድርጅቶች እራሳችሁን ማግለል ይጠበቅባችኋል። በማሕበርና በአማራ አንድነት ስም ከገንያጥና አፍራሽ ሃይል አማራ ስለሆነ ብቻ አብረን እንስራ ካላችሁ፤ ዓላማችሁ እንደሚበላሽ ከወዲሁ ልጠቁማችሁ እወዳለሁ። የምትከተሉት ፖሊሲና ጉዞ ከማን ጋር እንደሆነ ካልለያችሁ በስም አማራ ሌላ ጠላታችሁ እጎናችሁ ካስመጣችሁ “በሬ ካራጁ ይውላል” የሚለው የወላጆቻችሁ ምሰሌ እዚህ ላይ ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ። አርዳችኋላሁ፤ እገንጥላችኋለሁ፤አፈርሳችኋለሁ ከሚል በግልጽ እየነገራችሁ ካለው አፍራሽ ቡድን ጋር አንድነት መመስረት የናንትን ብስለት ያስገምታል።

ግንጣለን የሚያቀነቅኑ በተፈጥሮአቸው ስሜታቸውን ማሸነፍ ያቃታቸው፤ ጠንካራ የፖለቲካ ራዕይ እና አውቀት የጎደላቸው፤ ዘረኞች፤ የኢትዮጵያዊንትን መቀነት ያልታጠቁ፤ ቅናታቸው የላላባቸው፤ ተስፋ ተሎ የቆረጡ፤ የተሸነፉ፤ ሽንፈታቸውን ለመሸፈን መደበቂያ የሚፈልጉ፤ ተሸናፊዎችና ተምበርካኪዎች የሚከተሉት ፖለቲካ ምሽግ ነው። ወያኔዎች ትግራይ ትግርኚን በሁለተኛ ተጠባባቂ ስልት የያዙት ሲሸነፉ ሽንፈትን መቋቋም ሲያቅታቸው የሚያመልጡበት የተሸናፊዎ ዋሻ መሆኑን ማወቅ አያቅታችሁም። ኤርትራ ተገንጥላ ምን እየሆነች እንዳለች ህያው ምስክር ነው። መፍትሄው ፊት ለፊት በጠራ አገራዊ ፖለቲካ እየተመሩ አገራዊ እሴቶች እንዲከበሩ መታገልና ጠላትን ማሸነፍ አማራጩና ብቸኛው ስልት ነው። ወጣቶች ይህን ካላወቃችሁ አገሪቷ ሌሎች ልጆች መፈለግ አለባት

ሰላሙን ያብዛላችሁ!

ጌታቸው ረዳ getachre@aol.com